እኔ ማላጅ ነኝ

የመጽሐፍ ቅዱስ ንባብ — 1 ጢሞቴዎስ 2: 1-6

ልመናና ጸሎት ምልጃም ምስጋናም ስለ ሰዎች ሁሉ ስለ ነገሥታትና ስለ መኳንንትም ሁሉ እንዲደረጉ ከሁሉ በፊት እመክራለሁ . . . ። 1ኛ ጢሞቴዎስ 2: 1 - 2

ምናልባት "ጸሎት ነገሮችን ይለውጣል" የሚል ጽሑፍ ወይም ምልክት አይታችሁ ይሆናል። በእርግጥም አምላክ በዚህ ዓለም በሚሠራው የመንግሥቱ ሥራ የሕዝቡን ጸሎት እንደሚጠቀም በመጽሐፍ ቅዱስ እናያለን። ብዙ ምሳሌዎች እንደሚያሳዩት አምላክ ሕዝቦቹ በጸሎት የሚለምኑትን ነገር እንደሚመልስ እና እንደሚሰጣቸው ያሳያሉ።

ይህ ማለት ግን እግዚአብሔር ስለእኛ የሚኖር፣ ምኞታችንን የሚፈጽም እና የሚመልስልን ነው ማለት አይደለም። ጸሎታችን ለሕይወታችን እና በዚህ ዓለም ስላለው የመንግሥቱ ሥራ ከእግዚአብሔር ፈቃድ ጋር የሚስማማ መሆን አለበት (ማቴዎስ 6፡9-13፤ 1 ዮሐንስ 5፡14-15 ይመልከቱ)። አምላክ ጸሎታችንን የሚመልስልን ከፈቃዱ ጋር በሚስማማ መንገድ ቢሆንም፣ መልሱ ከምንጠይቀው የተለየ ሊሆን የሚችልበት ሁኔታ አለ። አንዳንድ ጊዜ የእግዚአብሔርን ፈቃድ ወይም እቅዱን ወይም መንገዱን እንኳን አንረዳውም (ኢሳይያስ 55)። አንዳንድ ጊዜ የእግዚአብሔር መልስ "አዎ፣ ግን ገና አይደለም" ወይም "በምናስበው መንገድ አይደለም" ወይም ደግሞ "አይሆንም" ሊሆን ይችላል። (ሉቃስ 22:42 ተመልከት።)

በ1ኛ ጢሞቴዎስ 2 ጳውሎስ አማኞች ስለ ሁሉም ማለትም "ነገሥታትና ባለ ሥልጣናት ስላሉት ሁሉ" እንዲማልዱ (እንዲጸልዩ) ያሳስባቸዋል ምክንያቱም "ይህ መልካም ነውና አምላካችንና አዳኛችንም በዚህ ደስ ያሰኛል"።

ስለ ሌሎች በታማኝነት ስንማልድ፣ በግላችን በእግዚአብሔር የማዳን ሥራ እንሳተፋለን። አምናለሁ እያንዳንዱ መንፈሳዊ ድል አንድ ሰው ሲጸልይ የተከሰተ ለመሆኑ ማረጋገጫ ነው።

ጌታ ሆይ፤ ለሌሎች በታማኝነት እንድንጸልይ እርዳን፣ ሰዎች አንተን እንዲያውቁህ እና በአንተ እምነት እንዲኖራቸው፣ ፈቃድህ በሰማይ እንደሆነች እንዲሁ በምድር እንድትሆን እለምንሃለው። በኢየሱስ ስም አሜን።

በ ዳን ጀንስማ የተጻፈ ከ**[https://todaydevotional.com/](https://todaydevotional.com/)** ድሕረ ገጽ ተወስዶ የተተረጎመ

ተማርኬአለሁ

የመጽሐፍ ቅዱስ ንባብ — ሮሜ 12:1

እንግዲህ፥ ወንድሞች ሆይ፥ ሰውነታችሁን እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኝና ሕያው ቅዱስም መሥዋዕት አድርጋችሁ ታቀርቡ ዘንድ በእግዚአብሔር ርኅራኄ እለምናችኋለሁ፥ እርሱም ለአእምሮ የሚመች አገልግሎታችሁ ነው። — ሮሜ 12:1

አንዳንድ ጊዜ ህይወቴን እንዲመራኝ እና እንዲቆጣጠረኝ በእግዚአብሔር ለመታመን ትግል ውስጥ ገብቼ ነበር። ሮሜ 12፡1 እራሴን ለጌታ መስጠት እንዳለብኝ ጠቃሚ ማሳሰቢያ ነበር። ይህ ጥቅስ በህይወቴ ያለውን ምህረቱንና ቸርነቱን አውቄ ራሴን ሙሉ በሙሉ ለእግዚአብሔር እንዳቀርብ ይሞግተኛል።

ለእግዚአብሔር መገዛት የአንድ ጊዜ ውሳኔ ብቻ አይደለም; በየቀኑ ፈቃዳችንን ከእግዚአብሔር ፈቃድ ጋር ለማስማማት ቃል መግባት አለብን። ይህም ፍላጎቶቻችንን፣ ፍርሃታችንን እና ምኞቶቻችንን መተው እና አምላካችን ሕይወታችንን እንደ ዓላማው እንዲመራን መጋበዝን ይጨምራል። እቅዶቻችንን አሳልፈን ለመስጠት እና የእግዚአብሔር መንገዶች ከፍ ያሉ እና ፍቅሩ የማይሻር መሆኑን ለመተማመን ትህትና እና እምነት ይጠይቃል።

ለእግዚአብሔር ስንገዛ እውነተኛ ነፃነት እና ሰላም እናገኛለን። ውጤቶችን ለመቆጣጠር እና በምትኩ የእግዚአብሔርን ሉዓላዊነት የምንቀበልበትን ሸክም እንለቃለን። እጅ መስጠት እግዚአብሔር በህይወታችን ተአምራቱን እንዲፈጽም በር ይከፍታል፣ ድክመቶቻችንን ወደ ጥንካሬ ትግሎቻችንን ወደ ፀጋው ምስክርነት ይለውጣል።

ለእግዚአብሔር ከመገዛት ጋር የምትታገሉ ከሆነ፣ በትጋት እንድትጸልዩ አበረታታችኋለሁ፤ የራሳችንን ህይወት መቆጣጠር እንደማንችል እግዚአብሔር ብቻ ሊቆጣጠር እንደሚችል እንድታዩ እንዲረዳችሁ ጠይቁት፤ እሱ እንደሚያስብልብ እና ለህይወታችሁ መልካሙን እንደሚፈልግ አውቃችሁ ፍርሃቶችህን፣ ህልሞችህን እና እርግጠኛ ያልሆኑትን ነገሮቻችሁን ለእርሱ ስጡት።

አባት ሆይ፣ እቅድህን እንድንታመን እና በየቀኑ ለፈቃድህ እንድንሸነፍ እርዳኝ። ህይወቴ የቸርነትህ እና የታማኝነትህ ምስክር ይሁን። ኣሜን።

በዳሬል ዳንሴይ የተጻፈ ከ**https://todaydevotional.com/** ድሕረ ገጽ ተወስዶ የተተረጎመ

የእግዚአብሔርን ኃይል በጸሎት ማመን

የመጽሐፍ ቅዱስ ንባብ — ያዕቆብ 5: 16

የጻድቅ ሰው ጸሎት በሥራዋ እጅግ ኃይል ታደርጋለች። —ያዕቆብ 5:16

አንድ የቅርብ ጓደኛዬ በጠና ታመመ። ሐኪሟ ተስፋ አልነበራቸውም፣ እናም ተስፋው እየጠፋ እንደሆነ ተሰማት። በተስፋ መቁረጥ ውስጥ ሆኜ ለጓደኛችን ፈውስ ለመፀለይ ሌሎች ጓደኞቼን እና ቤተሰቦቻችንን ሰበሰብኩ ፊታችንን ወደ ጸሎት አዞርኩ። እርግጠኛ ባንሆንም በአምላክ ኃይል በመታመን አጥብቀን መጸለይ ጀመርን።

ጓደኛችን በተአምር ማገገም ጀመች። ዶክተሮቹ በእሷ ድንገተኛ ለውጥ ተገረሙ፣ እግዚአብሔር ጸሎታችንን በፈውስ እንደመለሰልን ግልጽ ነበር። ይህም ጸሎት ኃይለኛ እንደሆነና አምላክ እውነተኛ ለውጥ ለማምጣት እንደሚጠቀምበት ያለኝን እምነት አጠናከረልኝ።

ጸሎት የአምልኮ ሥርዓት ብቻ አይደለም; ከፈጣሪያችን ጋር በቀጥታ የምንገናኝበት መስመር ነው። በጸሎት ጥልቅ ፍላጎታችንን፣ ፍርሃታችንን እና ተስፋችንን ለእግዚአብሔር እንገልፃለን። በጸሎት መጽናናኛን፣ ብርታትን እና ምሪትን እናገኛለን። መጽሐፍ ቅዱስ "የጻድቅ ሰው ጸሎት ኃይለኛና ውጤታማ ናት" በማለት ያስተምራል፤ አምላክም ሕይወትን ለመለወጥ ይጠቀምበታል።

ጸሎት ኃይሉ በእኛ እንዲሠራ በመፍቀድ ልባችንን ከአምላክ ፈቃድ ጋር ያስማማል። ፈውስ ያመጣል፣ በችግር ጊዜ መፅናናትን ይሰጣል፣ ለመከፈት የማይቻል የሚመስሉ በሮችን ይከፍታል። በጸሎት አማካኝነት አምላክን ወደ ጉዳያችን እንጋብዘዋለን፣ እንደ ሉአላዊ ፈቃዱ እንደሚፈጽም በመተማመን። እግዚአብሔር ይሰማናል እና ከምንጠይቀው ወይም ከምንገምተው በላይ ማድረግ ይችላል። ተአምራትን ለመስራት በኃይሉ በመታመን ጭንቀታችንን፣ ደስታችንን እና ፍላጎታችንን በፊቱ እናምጣ።

ጌታ ሆይ ስለ ጸሎት ስጦታ አመሰግንሃለሁ። ሁሌም እንደምታስብልን አውቀን በእምነት እና በመተማመን ወደ አንተ እንድንቀርብ እርዳን። በኢየሱስ ስም አሜን።

በዳሬል ዳንሌይ የተጻፈ ከ**https://todaydevotional.com/** ድሕረ ገጽ ተወስዶ የተተረጎመ

የጸና፣ የማይቋረጥ ጸሎት

የመጽሐፍ ቅዱስ ንባብ — ዘዳግም 10: 1-5, 10-11

እኔም እንደ ፊተኛው ጊዜ አርባ ቀንና አርባ ሌሊት በተራራው ላይ ተቀመጥሁ፤ እግዚአብሔርም በዚህ ጊዜ ደግሞ ሰማኝ፤ እግዚአብሔር ሊያጠፋህ አልወደደም። — ዘዳግም 10:10

ሙሴ የእግዚአብሔርን ትእዛዝ በድንጋይ ጽላት ሲቀበል ስለ ሕዝቡ አጥብቆ እንደጸለየ ያስረዳል። የእግዚአብሔርን ሕግ ለመቀበል ወደ ተራራ ሲወጣ ይህ ለሁለተኛ ጊዜ ነበር፤ ምክንያቱም እርሱ ለመጀመሪያ ጊዜ ባልኖረበት ጊዜ ሕዝቡ ኃጢአት ሠርተዋልና። ሕዝቡ በጣም ከፉ ኃጢአት ሠርተዋል ስለዚህም እግዚአብሔር ሊያጠፋቸው ዛተ፣ ነገር ግን ሙሴ ስለ እነርሱ ማለደ፣ እናም እግዚአብሔር የሙሴን ጸሎት ሰምቶ ሕዝቡን በጉዞአቸው ላካቸው። (በተጨማሪም ዘዳግም 9:7-29 ተመልከቱ።)

በቤተክርስቲያናችን፣ በቤተሰቦቻችን፣ በስራ ባልደረቦቻችን፣ በአጋሮቻችን እና በሌሎች የተጎዱ ወይም የጠፉ ነፍሳትን በመወከል ልባችን ሲጨነቅ እና የእግዚአብሔርን ጸጋ እየፈልግ እንጸልያለን። ያለማቋረጥ መጸለይ እና እንዲጸለይን ማድረግ ኃይለኛ ነው። ያለማቋረጥ እንጸልያለን (1ኛ ተሰሎንቄ 5፡17)። ሰዎች ለተቸገሩት፣ መኖሪያ ለሌላቸው፣ ለታመሙ፣ ለተራቡ ወይም ለተፈናቀሉ ሰዎች መማለዳቸው ያልተለመደ ነገር አይደለም። ከዚህም በላይ ሰዎች ንስሐ እንዲገቡና ይቅርታ እንዲደረግላቸው መጸለይ እንችላለን። እግዚአብሔር በሰዎች ሕይወት እና ሁኔታዎች ውስጥ በኃይለኛነት እንዲንቀሳቀስ እንተማመናለን ምክንያቱም እግዚአብሔር እንደሚወዳቸው እናውቃለን።

ያዕቆብ 5፡16 የጻድቅ ሰው ጸሎት ኃይለኛና ውጤታማ እንደሆነ ያረጋግጥልናል። እግዚአብሔር ይሰማናል፣ አዳኙ ኢየሱስ ስለ እኛ በታማኝነት ይማልዳል (ሮሜ 8፡34)። አስደናቂ ነው!

አባት ሆይ በተሰበረ ዓለማችን ውስጥ ስላሉ ሰዎች እና ሁኔታዎች እንድማለድ ስለጠራኸኝ አመሰግንሃለሁ። ኢየሱስ እንዳደረገው በታማኝነት እንድጸልይ እርዳኝ። አሜን።

በጌኒስ ፖይስ የተጻፈ ከ**https://todaydevotional.com/** ድሕረ ገጽ ተወስዶ የተተረጎመ

ትኩረት የሚሰጠው ወዳጅ እግዚአብሔር

የመጽሐፍ ቅዱስ ንባብ — 1 ሳሙኤል 1:1-20

ሐናም በልብዋ ትመረር ነበር፥ በእግዚአብሔር ፊት ጸለየች፥ ጽኑ ልቅሶም አለቀሰች። — 1 ሳሙኤል 1:10

ብዙ ሰዎች ከሐና ታሪክ ጋር በግል ሊዛመዱ ይችላሉ። የመካንነት ስሜታዊ፣ አእምሯዊ እና መንፈሳዊ ስቃይ ብዙዎች ጋር ያለ ነው፣ ብዙም ጊዜ እንደ አስጨናቂ ሚስጥር ቅርብ ነው።

ከሐና ታሪክ ውስጥ በጣም ቆንጆ ከሆኑት ነገሮች አንዱ እግዚአብሔር ለምትሰቃይበት እና ለጭንቀቶቿ የመለሰላት ምላሽ ነው። ሊቀ ካህናቱ ኤሊ ሰክራለች ብሎ ቢከሳትም አምላክ የሐናን ሥቃይ አይቶ እንክብካቤና ርኅራኄን አሳያት። የፍጥረት አምላክ ጣቱን ከመቀሰር እና ርቀቱን ከማስቀመጥ ይልቅ ሀናን እና ሀዘኗን አቅፎ ወደ እርሷ ቀረበ፣ ልቧን አዳመጠ፣ ለቅሶዋን ሰማ ሰማ፣ ነፍሷን ተንከባከባት በምላሹም ለሐናም የምትፈልገውን ወንድ ልጅ ሰጣት።

ሐና ነፍሳቸውን ለእግዚአብሔር ለማፍሰስ የማያፍሩ ሰዎች ምሳሌ ናት ምክንያቱም እርሱ እንደሚሰማ፣ እንደሚያደምጥ፣ እንደሚያስብ፣ እና ጥልቅ ህመሞችን እንኳን እንደሚያስወግድ ያውቃሉ።

የክርስቶስ ተከታዮች እንደመሆናችን መጠን ፍቅሩንና ርኅራኄውን በጭንቀት ውስጥ ላሉ ሰዎች ማካፈል እንችላለን። ጩኸታቸውን ሰምተን ሸክማቸውን እንድንሸከም መርዳት፣ ከእነሱ ጋር መጸለይ እና ሁላችንን በሚወደው አምላክ ማጽናኛ እንዲያገኙ መርዳት እንችላለን።

የተወደድክ አምላክ ሆይ! ለሚጎዱት ሁሉ እንድትቀርብ እና ሐና የተሰማትን አይነት ሥቃይ ውስጥ እያለፉ ያሉትን ሁሉ እንድታጽናና እለምንሃለው። እንደምትሰማቸው እና እንደምትንከባከባቸው ይወቁ፤ በምሕረትህ እና በጸጋህ ነፍሳቸውን ሙላ አርካቸውም በኢየሱስ ስም ለመንኩህ። አሜን!

በቤን ማክናይት የተጻፈ ከ**https://todaydevotional.com/** ድሕረ ገጽ ተወስዶ የተተረጎመ